በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

ሐምሌ /2017 ዓ.ም

ሐምሌ 5
በመትከል ማንሰራራት!



ኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ የም/ቤቱን የ2017 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በመገምገም የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ተወያይቶ አፅድቋል።

Boordiin Daayirektarootaa Mana Maree Daldalaafi Waldaalee Sekteraalee Itoophiyaa gabaasa raawwii hojii bara bajataa 2017 gamaggammuun.karoira bara bajataa 2018 irratti mari'achuun raggaasiseera.









ማውጫ

የምክር ቤቱ ቦርድ ስብሰባ————————--1

የምክር ቤቱ አረንጓዴ አሻራ ግብር——--1-2

ePPD ውይይት————————————3

ከሮማኒያ አምባሳደር ጋር ውይይት———3

ፕሬዚዳንቱ ከአልጀሪያ አምባሳደር————4

ዋ/ጸሐፊው ከትሬድ ማርክ አፍሪካ ጋር——4

የኦሮሚያ ን/ምክር ቤት ቦርድ ስብሰባ——-5

የምክር ቤቱ የመቄዶኒያ ጉብኝት————-5

የቦርድ አባላት ጅግጅጋ አቀባበል————-6

ከአሜሪካ አምባሳደር ጋር ውይይት———-6

ከሶማሌ ም/ርዕሰ መስተዳድር ውይይት—7

የተሸከርካሪ መገጣጠሚያ ጉብኝት———8

የችግኝ ተከላ በፋፈን ዞን————-—8-9

ዋና ጸሐፊ ከሩሲያ ፌደሬሽን ጋር———--10

ከአፍሪካ ልማት ባንክ ጋር ውይይት——-11

ከደቡብ አፍሪካ አምባሳደር ጋር ውይይት—11

ዋና ጸሐፊ ከእናት ባንክ ጋር ውይይት——12

ዋ/ጸሐፊ ከአፍሪካ ት/ቤቶች ማኅበር ——13

ም/ዋ/ጸሐፊ ከዮርዳኖስ ተጠሪ ጋር ——--14

ቢዝነስና ሰብዓዊ መብት ወርክሾፕ——-1516

ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ችግኝ ተከላ—-———17

የተለያዩ ምክር ቤቶች ችግኝ ተከላ——18-20

አድራሻ————————————--22

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና የንግዱ ማኅበረሠብ የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ተካሄደ።

ሐምሌ 5/2017 ዓ.ም "የንግዱ ማኅበረሠብ የአረንጓዴ አሻራ ቀን" በሚል ነው በሀገር አቀፍ ደረጃ የችግኝ ተከላ ፕሮግራሙ የተካሄደው።

በአዲስ አበባ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ደኤታ ዶክተር አብዱልሀኪም ሙሉ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር እንዲሁም የአዲስ አበባ፣ የኦሮሚያ እና የሸገር የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የሥራ አመራር ቦርድ አባላትና ሠራተኞች እንዲሁም ከንግዱ ማኅበረሠብ የተውጣጡ አካላት በተገኙበት በእንጦጦ ፓርክ ተካሂዷል።





በተከላ ፕሮግራሙ ላይም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ ደክተር አብዱልሀኪም ሙሉ መላው የንግዱ ማኅበረሠብ የአረንጓዴ አሻራ ሥራን እንደ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሠረት በመውሠድ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባው አሥገንዝበዋል።





የቀጠለ.....

ለአየር ንብረት ለውጥ መከላከልና አካባቢ ጥበቃ፣ ለዘላቂ የአረንጓዴ ልማት መሣካት ትልቅ አሥተዋጽኦ ለሚያበረክተው የአረንጓዴ አሻራ መትከል ብቻ ሣይሆን መንከባከብም ዋነኛው ተግባር መሆን እንደሚገባው አሣሥበዋል።



የአረንጓዴ አሻራ ሥራም ትኩረት የተሠጠውና የንግዱ እየተገበረው ያለው ተግባር ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብሥብ አባፊራ አባጆቢር በበኩላቸው የግሉ ዘርፍ የአረንጓዴ አሻራ ሥራን በባለቤትነት በመውሠድ ተግባራዊ እያደረገ ሲሆን ችግኝ ተከላ ለንግዱ ዘርፍ ትልቁ ትኩረት መሆኑን አንሥተዋል።



ምክር ቤቱ በተሻለ መልኩ እየተገበራቸው ካሉ የሪፎርም ሥራዎች አንዱ ማኅበራዊ ኃላፊነትን መወጣት መሆኑን ያነሡት አቶ ሰብስብ ማኅበረሠብም በየአካባቢው



"በመትከል ማንሠራራት" የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር በእንጦጦ ፓርክ ሲካሄድ ከምክር ቤቶች የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በተጨማሪ የተለያዩ ድርጅቶች ሥራተኞች እና ባለሙያዎችም ተሣትፈዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

የንግዱ ማኅበረሰብ 7ኛ ዙር የአረንጓዴ አሻራ

የችግኝ ተከላ መርሀ-ግብር

በመትከል ማንሰራራት!



አዲስ አበባ: እንጦጦ

ሐምሌ 5/ 2017 ዓ.ም

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና BEIC ፕሮጀክት electronic Public-Private Dialogue (ePPD) እና የ (Public-Private Dialogue (PPD)) ሞዴል አተገባበር ሂደት ላይ ተወያይተዋል።

ሚኒስቴሩ ከኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በመተባበር የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ውይይትና የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ውይይት ሞዴል





አፈጻጸምን ለመገምገም በBEIC ፕሮጀክት ሂደት ላይ ነው የተወያዩት።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር አብዱልሀኪም ሙሉ እና የምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) አሰራሩ ለፖሊሲ ቀረፃ፣ ለተሻሻለ የንግድ አካባቢ እና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎዎች እንዴት አስተዋጽኦ እያበረከተ እንዳለ አብራርተዋል።





ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር አብዱልሀኪም ሙሉ እና ዋና ፀሃፊው ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ electronic Public-Private Dialogue (ePPD) እና የPublic-Private Dialogue (PPD) ሞዴል እድገት ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ወሳኝ ዘዴዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ ኅብረትና ሶማሊያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ከሆኑት የሮማኒያ አምባሳደር ጁሊያ ፖታኪ ጋር ተወያይተዋል።





ዶ/ር ቀነኒሳ የምክር ቤታቸውን እንቅስቃሴ፣ የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ ለውጦች እና በሁለቱ ሀገራት መካከል የበለጠ የንግድና ኢንቨስትመንት እድችን ሊፈጥሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ለአምባሳደሯ አብራርተውላቸዋል።

አምባሳደር ጁሊያ ፖታኪ የሁለቱ ሀገራት የንግድ እና የኢኮኖሚ ድርጅቶች ትብብር አስፈላጊነት ላይ አጽንኦት ሰጥተዋል።

የንግድ ግንኙነቶች ለሁለቱም ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት የበለጠ ማቀላጠፍ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ክቡር አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር በኢትዮጵያ የአልጄሪያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አምባሳደር ከሆኑት ዶክተር መሀመድ ካሊድ ጋር በጽህፈት ቤታቸው ተወያይተዋል።



የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ክቡር አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር በኢትዮጵያ የአልጄሪያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አምባሳደር ከሆኑት ዶክተር መሀመድ ካሊድ ጋር በጽህፈት ቤታቸው ተወያይተዋል። ሁለቱ ታላፊዎች በሁለቱ ሀገራት መካከል ስላለው የንግድና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ተስፋዎች ተወያይተዋል።

ኢትዮጵያ እና አልጄሪያ የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ እና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ቢኖራቸውም ኢኮኖሚያዊ እና የንግድ ትስስራቸው ጥሩ እንዳልሆነ አውስተው የሁለቱም ሀገራት የንግድ ምክር ቤቶች የሀገራቱን የንግድና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ለማጠናከር ተባብሮ መስራት አለባቸው ብለዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሪዘዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር በሁለቱም ሀገራት የንግድ ግንኙነት ውስጥ ያሉትን ምቹ ሁኔታዎችና ተስፋ ገልፀው፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከአልጄሪያ የንግድ ምክር ቤት ጋር ለመተባበር ቁርጠኛ መሆኑን ገልጸዋል።



በኢትዮጵያ የአልጄሪያ አምባሳደር እና ኮሚሽን ቋሚ ተወካይ ዶ/ር ሞሃመድ ተመራጭ መሆኗን እንዲሁም የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ ሰፊ ሁለቱ ወገኖች በንግድ፣ ትርኢቶች እና በሌሎች በርካታ ኢንዱስትሪዎች ለሚደረጉ የቢዝነስ ጥግንኙነቶች ተግባራዊነት አምባሳደሩ አስረድተዋል።የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ፣ ዶ/ር ቀነኒሳ እና የአልጄሪያ ተልዕኮ ዲፕሎማቲክ አታሼ ጋህድር አብደራኦፍ በውይይቱ ላይ ተገኝተዋል።

በአፍሪካ ህብረት እና በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ካሊድ አልጄሪያ ለቡና እና ሌሎች የኢትዮጵያ ምርቶች መዳረሻነት በሁለቱም ሀገራት ማብራሪያ ሰጥተዋል።



በኢንቨስትመንት፣ በንግድ መተባበር እዳለባቸውም ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከትሬድ ማርክ አፍሪካ ጋር አብሮ መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተወያየ።።

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምከር ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የተመራው የማኔጅመንት ቡድን ከትሬድ ማርክ አፍሪካ የኢትዮጵያ ፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ እውነቱ ታዬ ጋር በጽህፈት ቤታቸው በሁለትዮሽ ሊሰሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት አድርጓል።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ቀደም ሲል በአንድ መስኮት አገልግሎት ትግበራ ላይ ከአፍሪካ ትሬድ ማርክ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ አገልግሎቱን በድጂታል መስጠት በመቻሉ አገልግሎቱን ከማዘመኑም ባሻገር የአገልግሎት የንግዱን ማህበረሰብ ጊዜና ወጪ ለመቆጠብ አስረድተው፣ ለዚህም በም/ቤቱ ስም አመስግነዋል።



ለወደፊቱም ም/ቤቱ ትኩረት አድርጎባቸው የለያቸውን የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ሊያሻሽሉና አቅማቸውን የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በፋይናንስ እንዲደግፉ ለዳይሬክተሩ ጥያቄአቸውን አቅርበዋል። የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት አሁን ላይ ከወትሮው በተሻለ ሁኔታ የግሉን ዘርፍ ፍላጎት ለማሟላትና ከመንግስት ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግንኙነት ለማሳለጥ እንዲሁም እየመጣበት ባለው ብርቱ ፉክክር ውስጥ ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆን እየሰራ ነው ያሉት ዋና ፀሐፊው ለዚህ ደግሞ የአጋር ድርጅቶች እገዛ ያስፈልገዋል ብለዋል።

የትሬድ ማርክ አፍሪካ የኢትዮጵያ ፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ እውነቱ ታዬ በበኩላቸው ቀደም ሲል የፋይናንስ ድጋፍ የተደረገለት የአንድ መስኮት አገልግሎት አሁን ያለበት ሁኔታ አስደሳች መሆኑን ገልፀው ሌሎች በም/ቤቱ ተቀርፀው የፋይናንስ ድጋፍ የሚጠየቅባቸው ፕሮጀክቶች በለጋሽ ድርጅቶች ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ በቀጣይነታቸው፣ በሚያመጡት አዎንታዊ ለውጥና ም/ቤቱ ፕሮጀክቶቹን በባለቤትነት ተግባራዊ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት በደንብ የሚገልፁ መሆን እንዳለባቸው አስረድተዋል። በዚህ መሰረት ለሚቀርቡ ፕሮጅክቶች በተቻለ መጠን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውንም አሳውቀዋል።

የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 2ተኛ የሥራ ዘመን 12ኛ መደበኛ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል ተካሂዷል።

የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 2ተኛ የሥራ ዘመን 12ኛ መደበኛ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል አካሄደናል::

ስብሰባው ላይ የ2017 በጀት ዓመት የክንውን ሪፖርት በመገምገም የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ተወያይተን አፅድቀናል ::

ሰብስብ አባፍራ አባጆቢር



Har'a wal-boordii idilee 12ffaa bara 2ffaa Mana Daldalaa fi lee Sekteraalee



gahiin Marsaa hoji Maree Waldaa-Oromi-yaa Fin-finee, Ho-Walgahii baajata 2018 irratti



teela Hilton keessatti geggeesineera. har'aa irratti gabaasa raawwii hojii bara 2017 gamaaggamuun karoora bara baajata mari'annee raggaasifneerra

Sabsib Abbaafiraa Abbaajoobir

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሥራ ኃላፊዎች መቄዶኒያ በጎ አድራጎት ማኅበርን ጎበኙ።

የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሣ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር) እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ናቸው ማኅበሩን የጎበኙት።







ምክር ቤቱም ለበጎ አድራጎት ማኅበሩ የግማሽ ሚሊየን ብር የአይነት እና የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።



ምክር ቤቱ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እንደ መቄዶኒያ ካሉ በጎ አድራጎት ተቋማት ጋር በትብብር የሚሠራ ምክር ቤት መሆኑን የገለጹት ዶክተር ቀነኒሣ በቀጣይም ለማኅበሩ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። የንግዱ ማኅበረሠብ ለመቄዶንያ በጎ አድራጎት ማኅበር የሚያደርገውን ድጋፍ እንዲያጠናክር የማኅበሩ መሥራች ክቡር ዶክተር ቢኒያም በለጠ አሣሥበዋል።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ ለሁለት ቀን የስራ ጉብኝት የሶማሌ ክልል መዲና ጅግጅጋ ሲገቡ የተደረገ አቀባበል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ ለሁለት ቀን የስራ ጉብኝት የሶማሌ ክልል መዲና ጅግጅጋ ገብተዋል።



የዳይሬክተሮች ቦርድ አመራሮች በቆይታቸዉ የክልሉን ርዕሰ መስተዳድር ጨምሮ ከተለያዩ የመንግስት አካላት ጋር



የንግድ ም/ቤቶች ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ይመክራሉ። በም/ቤቱ ፕሬዘዳንት ሰብስብ አባፍራ አባጆቢር የተመራዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ልዑክ ጅግጅጋ አዉሮፕላን ማረፍያ ሲደርስ በሱማሌ ክልል ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የቦርድ አመራሮች አቀባበል ተደርጎላቸዋል።









በዋና ፀሀፊው በዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የተመራ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ልኡካን በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኤርቪን ማሲንጋ እና ሌሎች የኤምባሲው የንግድና ንግድ ተወካዮች ጋር ውጤታማ ውይይት አድርገዋል።



ውይይቱ በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ መካከል ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ማጠናከር እና የሁለትዮሽ ግንኙነትን ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው።

በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ ያሉ የንግድ ድርጅቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግና ማራኪ እና ምቹ የንግድ ሁኔታ ለመፍጠር ሁለቱም ወገኖች በጋራ ለመስራት ተስማምተዋል። የውይይቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ከዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ጋር የተጣጣመ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፣ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የኢኮኖሚ ውህደት፣ ዲጂታል እና ፋይናንሺያል እውቀት፣ የECCSA እና የአባል ምክር ቤቶቹ እና ማህበራት የዲጂታል ትስስር እና የግሉ ሴክተር ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ናቸው።አምባሳደር ኤርቪን ማሲንጋ በኢትዮጵያ ያለውን የንግድ ስነ-ምህዳር ለማሻሻል ከECCSA ጋር ለመተባበር ያላቸውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል። ዶ/ር ቀነኒሳ በበኩላቸው በኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት እድሎች እያደጉ መምጣታቸዉን አጽንኦት ሰጥተዋል አንስተዋል።

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፍራ አባጆቢር ተመርቶ ለ2 ቀን የስራ ጉበኝት ወደ ሶማሌ ክልል የተጓዘዉ የም/ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ልዑካን ቡድን በዛሬዉ ዕለት ከሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኢብራሂም ዑስማንፋራህ ጋር ተወያይቷል።

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፍራ አባጆቢር ተመርቶ ለሁለት ቀን የስራ ጉበኝት ወደ ሶማሌ ክልል የተጓዘዉ የም/ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ልዑካን ቡድን በዛሬዉ ዕለት ከሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኢብራሂም ዑስማንፋራህ ጋር ተወያይቷል።







በዉይይቱም ላይ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፍራ አባጆቢር ከም/ቤቱ ታሪካዊ ዳራ በመነሳት ዛሬ ያለበትን ሁኔታ እና ተልዕኮዉን አብራርተዋል።



በተለይም አሁን ላይ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች እየመጣባቸዉ ካለዉ ብርቱ ፉክክር አንፃር ተወዳዳሪ ለመዉጣት በተደራጀ መልኩ መንቀሳቀስና ዘመኑን የዋጀ ዕዉቀት መታጠቅ እንዳለባቸዉ ገልፀዉ ለዚህ ደግሞ በየደረጃዉ ባሉ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት አባል መሆን አለባቸዉ ብለዋል።

ዘርፍ ማህበራት ምንም እንኳን የግሉ ዘርፍ ድምፅ ቢሆኑም የንግዱ ማህበረሰብ መንግስት በሚያወጣቸዉ የህግ ማዕቀፎች ዉስጥ ህጋዊ ንግድ በመስራት የሚጠበቅባቸዉን ህጋዊ ግብር እንዲከፍሉ የሚያድረጉና ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዙ የመንግስት ቀኝ እጅ ነዉ ለማለት ይቻላል።



ስለሆነም የሱማሌ ክልል ደግሞ በንግድ መዳረሻነቱ ከጎሮቤት ክልሎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከጎሮበት አገሮች ጋርም ጠንካራ የንግድ ትስስር ስላለዉ የንግዱን ማህበረሰብ የሚያሰባስብ ጠንካራ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ያስፈልገዋል። ለዚህ ደግሞ የክልሉ መንግስት ለሱማሌ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ተገቢዉን ድጋፍ እንዲያደርግና እንዲያበረታታ አቶ ሰብስብ ለምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ጥያቄአቸዉን አቅርበዋል።

የሶማሌ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኢብራሂም ዑስማንፋራህ በበኩላቸዉ የክልሉ መንግስት በክልሉ የንግድ ስራዉ በተደራጀ መልኩ እንዲመራ ም/ቤቱ እንዲጠናከር እንደሚፈልግ ገልፀዉ እኛም እንደክልላዊ መንግስት ተገቢዉን ድጋፍ እናደርጋለን; የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤትም ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለበት ብለዋል። በአሁኑ ሰዐትም የክልሉ መንግስት ለክልሉ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የራሱ ህንፃ መስርያ ቦታ ሊሰጠዉ እያመቻቸ መሆኑንም ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ገልፀዋል።



በክልሉ ከለዉጡ ወዲህ በተረጋገጠዉ ፍፁም ሰላም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ሊኖርበት የሚመኝ ሆኗል ያሉት ም/ል ርዕሰ መስተዳድሩ ከዚህ ቀደም ያልተለመደ የግብርና ስራም ተጀምሯል ብለዋል። አሁንም ሰፊና ሊለማ የሚችል ሰፊ መሬት ያለን ስለሆነ በዘርፉም ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸዉን እንዲያፈሱና ለዚህም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት አምባሳደር ሆኖ እንዲያስተዋዉቅ ጥሪ አቅርበዋል።

በዉይይቱ ላይ የሱማሌ ክልል ምክትል የንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሀሰን የሱፍ የም/ል ርዕሰ መስተዳድሩ አማካሪ አቶ ከማል ሼህመሀመድ እና የሱማሌ ክልል የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚዳንት አቶ አህመድ ሀሰን ሸርማርኬ እና የቦርድ አባላት ተገኝተዋል።

የዘመናዊ አዉቶሞቢሎችና ቀላል የጭነት ተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ ጉብኝት በሶማሌ ክልል

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የተመራዉ የም/ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ልዑክ ከሱማሌ ክልል የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ምክትል ኃላፊና የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የቦርድ አባላት ጋር በመሆን በSAHID MI Engineering የሚሰራ የከባድ መኪና አካል ማምረቻና መገጣጠሚያ እና SWUEYS MOTERS COMPANY የተሰኘ የዘመናዊ አዉቶሞቢሎችና ቀላል የጭነት ተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ ጎብኝቷል።







አምራች ኢንዱስትሪዉ በሱማሌ ክልል ላይ እንደሚገኝና በመንግስት በኩል ሊደረግላቸዉ እንደሚገባ አቶ ሰብስብ አሳስበዋል።

በጉብኝቱ ወቅት በአበረታች ሁኔታ ተገቢዉ ድጋፍ የተሰማቸዉን ደስታ ገልፀዉ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በታሪኩ ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ክልል ወርዶ የስራ ጉብኝት አድርጎ የግሉን ዘርፍ ማነቃቃትና ለማበረታታት መጀመሩ ታሪካዊና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባ ተግባር ነዉ ብለዋል።





በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የተመራዉና በሶማሌ ክልል የስራ ጉብኝት







እያደረገ ያለው የምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ልዑክ በሶማሌ ክልል ፋፋን ዞን ሸበሌ ወረዳ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር አከናውኗል።

በመርሀ ግብሩም የሶማሌ ክልል የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱልሀኪም ሼክሀሰን እና ምክትል ኃላፊ አቶ ሀሰን የሱፍ እንዲሁም የክልሉ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ አህመድ ሀሰን ሸርማርኬ እና ሌሎች የቦርድ አባላት ተገኝተዋል።





የልዑካን ቡድኑ በክልሉ ለሁለት ቀናት የስራ ጉብኝት እያደረገ ሲሆን በሁሉም ክልሎች የንግዱ ማኅበረሰብ በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የሚያደርገውን ተሳትፎ እንዲያጠናክርም ፕሬዚዳንቱ አቶ ሰብስብ አባፊራ በመርሀ ግብሩ ላይ አሳስበዋል።

በሶማሌ ክልል የስራ ጉብኝት እያደረገ ያለው የምክር ቤታችን የዳይሬክተሮች ቦርድ ልዑክ በሶማሌ ክልል ፋፋን ዞን ሸበሌ ወረዳ ሸበሌ ርዞርት የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር አከናውኗል።

በመርሀ ግብሩም የሶማሌ ክልል የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱልሀኪም ሼክሀሰን እና ምክትል ኃላፊ አቶ ሀሰን የሱፍ እንዲሁም የክልሉ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ አህመድ ሀሰን ሸርማርኬ እና ሌሎች የቦርድ አባላት ተገኝተዋል።







የልዑካን ቡድናችን በክልሉ ለሁለት ቀናት የስራ ጉብኝት እያደረገ ሲሆን በሁሉም ክልሎች የንግዱ ማኅበረሰብ በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የሚያደርገውን ተሳትፎ ተጠናክሮ ቀጥሎዋል::





Guyyaa har'aa Boordiin Daayirektaroota Mana Maree keenyaa kan daawwannaa hojii Naannoo Somaaleetti taasisaa jiru sagantaa dhaabbii biqiltuu miila magariisaa Godina Somaalee Zoonii Faafan Aanaa Shebele Riizoortii Aanaa Shebeleetti gaggeessee jira.

Sagantaa kana irratti Itti Gaafatamaan Biiroo Daldalaa fi Indaastirii Naannoo Somaalee Atoo Abdulhaakim Sheekhaa-saanii fi Itti aanaa Itti Gaafatamaa Atoo Hasan Yuusuf akkasumas Pireezidaantiin Mana Maree Daldalaa fi Waldaalee Damee Naannichaa Atoo Ahimad Hasan Shermarkee fi miseensonni boordii biroo argamaniiru.





Jilli keenya daawwannaa hojii guyyoota lamaaf naannichatti kan gaggeeffamu yoo ta’u, sagantaa miila magariisaa naannolee hunda keessatti hirmaannaa hawaasa daldalaa cimsuu itti fufeera.

ፖለቲካ አይደለም!



ለሆነ አካል የምንውለው ውለታ አይደለም! ለሰው ብለን የምናደርገው ቀላል ነገርም አይደለም! ከምንገምተው በላይ ትልቅ አንድምታ ያለው ሀገራዊ ጉዳይ ነው!! ለነገው ትውልድ ቅሪት የማስቀመጥ፣ ነገ የተሻለች ኢትዮጵያን ለትውልድ የመገንባት፣ ዛሬን ተሻግረን ነገን ማሰብ ነው!! ተስፋን በትውልድ ቅብብሎሽ መሃል ማኖር ነው!! ሀገርን የመውደድ ምልክት ነው!! ትላንት አባቶቻችን ያቆዩልንን የተከበረች ሀገር እኛም በጊዜያችን በጣም የተሻለች ሀገር ለቀጣዩ ትውልድ የማስረከብ ትልቅ አሻራ ነው!! ሀገር የወል እውነታችን ናት።

የሁላችንም ቤት ናት። በዘር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በሀይማኖት፣ በትውልድ አከባቢ ሳንገደብ ለኢትዮጵያችን የምናኖረው ትልቅ ታሪክ ነው። ይህ ለሀገር የምንከፍለው ዋጋ ነው!


ይህ ግን የማያልፍ ቋሚ ቅርስ ነው!! ይህ ኢትዮጵያችንን በአለም ከፍ የማረግ ተግባር ነው!! ይህ በፈተና መሃል የምናሳካው ጣፋጭ ድል ነው!! ይህ ስምን ከመቃብር በላይ የምናረግበት የታሪክ መወደሻ መንገድ ነው!! ይህ እኛ አስቀምጠን አልፈን ነገ ትውልድ ስማችንን እየዘከረ የሚኖርበት ነው! ይህ ለኢትዮጰያ ነው!!

ችግኝ እንተክላለን!!!!

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) በኢትዮጵያ ከሩሲያ ፌዴሬሽን ተወካዮች ጋር ተወያይተዋል።

ሁለቱም ወገኖች በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድና የኢንቨስትመንት አቅም ማጎልበት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ተወያይተዋል።





ዋና ጸሃፊው በኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን፣ በሀገሪቱ ቅድሚያ በተሰጣቸው በርካታ ዘርፎች ላይ የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎችን አንስተዋል።

በኢትዮጵያ ለሚሰማሩ የውጭ ባለሃብቶች ማበረታቻዎችን እና አሁን ያለውን የኢንቨስትመንት እድል በተለይም እንደ ግብርና፣ ማዕድን፣ አይሲቲ እና ሌሎችም ትኩረት የተሰጣቸውን ዘርፎች አብራርተዋል።



ዶ/ር ቀነኒሳ የሁለቱ ሀገራት የረጅም ጊዜ የንግድ፣ የህዝብ ለህዝብ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መጠናከር እንዳለበት ጠቁመው፣ የንግድ ድርጅቶቻቸው ለጋራ ልማት በጋራ መስራት አለባቸው ብለዋል።

የሩስያ ፌዴሬሽን የንግድ ኮሚሽነር ዶክተር ያሮስላቭ ቪ. ታራሲዩክ የሩስያ ኩባንያዎች እና ቢዝነሶች ሊሰሩባቸው እና ኢንቨስት ሊያደርጉባቸው በሚችሉባቸው ዘርፎች ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ሩሲያ ለረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ አጋር እንደነበረች ገልጸው፣ ግንኙነቱ እንዲዳብርና ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲያድግ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትና የሩሲያ አቻው በትብብር መስራት እንደሚያስፈልጋቸው ገልጸዋል።

ኮሚሽነር ያሮስላቭ ቭ የሩስያ ቢዝነሶች በኢትዮጵያ በተለይም በሃይል፣ በጤና አጠባበቅ፣ በግንባታ፣ በኤሌክትሪፊኬሽን፣ በማዳበሪያ እና በሌሎችም ዘርፎች ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል። የሩስያ ፌዴሬሽን የግብርና ሚኒስቴር ተወካይ የሆኑት አንድሬ ስታይዝኪንም በውይይቱ ላይ ተገኝተዋል.

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የኢትዮጵያ ዋነኛ የልማት አጋር ከሚባሉት አንዱ ከሆነው የአፍሪካ ልማት ባንክ ጋር የአጋርነት ስትራቴጂ የግማሽ ዘመን አፈፃፀም ዙርያ ውይይት አድርጓል።





የውይይቱ አላማም በአጋርነት ስትራቴጂው በተካተቱ ሴክተሮች ውስጥ የግሉ ዘርፍ ሚና ምን እንደሚመስል ለመገምገምና በቀረው የስትራቴጂክ የትብብር ጊዜው ማለትም እ.ኤ.አ. እስከ 2027 ድረስ በተመረጡ ሴክተሮች የግሉ ዘርፍ መሳተፍ እንዳለበት ለማበረታታትም ነው።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እስከ ዛሬ ድረስ የልማት አጋሮች ከመንግስት ጋር ብቻ ሲሰሩ እንደነበር በመግለፅ ም/ቤቱ አሁን ላይ የግሉን ዘርፍ አቅም ለመገንባትና በልማት አጋሮች የሚመጡ ፈንዶችን በስራ ላይ የማዋል ቁመና እንዲኖራቸው ለማድረግ እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል።



የአፍሪካ ልማት ባንክ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ሚስተር ናትናኤል በበኩላቸው የትዮጵያ መንግስት በአሁኑ ወቅት የኢኮኖሚ ዘርፎቹን ለውጭ አገራት ክፍት በማድረጉ የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመውጣት እና ከልማት አጋሮች ጋር ለመስራት ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ገልፃወል።



የአፍሪካ ልማት ባንክ የግሉን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ለማጎልበት እና በአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ ለማሻሻል በም/ቤቱ የሚሰሩ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይደግፋል ያሉት ባለሙያው. በተለይም ለአሰነስተኛና መካከለኛ ቢዝነሶችና ለአግሮ ማኑፋክቸሪንግ ልዩ ትከረት እንደሚሰጥ ጠቁመዋል።



በዋና ፀሐፊው ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የተመራው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ልዑክ በኢትዮጵያ የደበብ አፍሪካ ሪፐብሊክ አምባሳደር ኖንሴባ ናንሲ ሎሲ ጋር የሁለቱን አገሮች የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስርን ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ውጤታማ ውይይት አድርጓል።



በውይይቱም በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በህጋዊ የቢዝነስ ስራዎች ላይ በመሰማራት ለሁለቱም አገሮች ዕድገት አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው መጠናከር እንዳለበት አፅንኦት ተሰጥቶታል።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከእናት ባንክ የስራ ኃላፊዎች ጋር ተወያዩ።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከእናት ባንክ የስራ ኃላፊዎች ጋር ተወያዩ።

ሁለቱ አካላት የሴቶችን አቅም በመገንባት፣ በስልጠና፣ በፋይናንስ አቅርቦትእንዲሁም በተለያዩ የንግድ ስራዎች ለተሰማሩ ሴቶች የገበያ እድሎችን በማመቻቸት ረገድ በጋራ ለመስራት ተወያይተዋል። በምክር ቤቱ እንቅስቃሴ እና የትኩረት አቅጣጫዎች ዙሪያም ዋና ጸሐፊው ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ አብራርተውላቸዋል።




ምክር ቤቱ ባካሄደው ሪፎርም የሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞችን

ለመደገፍናአቅማቸውን ለመገንባት ለብቻው የስራ ክፍል በማደራጀት በትኩረት እየተሰራ መሆኑንም ዶክተር ቀነኒሳ ጠቁመዋል።

በምክር ቤቱ የቢዝነስ አመራር አካዳሚ በኩልም አስፈላጊውን የአቅም ግንባታስልጠናዎች ለመስጠት እና በሴቶች ላይ የሚስተዋሉ እንቅፋቶችን ለማስወገድ ከእናት ባንክ ጋር በትብብር ለመስራት የምክር ቤቱ ፍላጎት መሆኑን አብራርተዋል።

በሌላ በኩል ምክር ቤቱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት በሚከናወኑየምርትና አገልግሎት ማስተዋወቂያ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲሁም ሌሎች የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይቶች ሴቶች የገበያ እድል እንዲያገኙ በትኩረት እንደሚሰራም ነው የገለጹት።

የእናት ባንክ የወሜን ባንኪንግ ሶሉሽን (Women BankingSolution) ዲፓርትመንት ዳይሬክተር ተናኘ ባሳ በበኩላቸው ባንኩ የሴቶችን አቅም በማሳደግ፣ በፋይናንስ አቅርቦት፣ የብድር አገልግሎትን በማመቻቸት እንዲሁም ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የስራ እድል በማመቻቸት ረገድ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍማኅበራት መስራት ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት እንደሚያስችል ተናግረዋል።



የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ከስልጠና፣ አካታች የፋይናንስ አቅርቦት ባለፈ ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመቅረፍ ከመንግስት ተቋማት ጋር በመነጋገር የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የውይይት ፕሮግራሞችን(Public-Private Dialogue) ማዘጋጀትና ችግሮቻቸው መፍትሄ እንዲያገኙ ለማስቻልም በጋራ እንደሚሰራ በውይይቱ ላይ ተነስቷል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከአፍሪካ ቢዝነስ ትምህርት ቤቶች ማኅበር ዋና ዳይሬክተር ላና ኤራምሊ ጋር ተወያዩ።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከአፍሪካ ቢዝነስ ትምህርት ቤቶች ማኅበር ዋና ዳይሬክተር ላና ኤራምሊ ጋር ተወያዩ።



በአህጉሪቱ ጠቃሚነት፣ ተፅእኖ እና ዘላቂነት ላይ አጽንኦት በመስጠት፣ የአፍሪካ የንግድ ትምህርት ቤቶች ማህበር ከአህጉሪቱ ከፍተኛ ጥራት ያለው የንግድ ትምህርት ተቋማት ማኅበር አንዱ ለመሆን ይፈልጋል።

"የአፍሪካ ቢዝነስ ት/ቤቶች ማህበር (AABS) በብዙ የአፍሪካ ሀገራት እየተንቀሳቀሰ ሲሆን በኢትዮጵያ በተለይም ከኢትዮጵያ ንግድና ዘር ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በአገር ውስጥ ዕውቀት እና በአለም አቀፉ ነባራዊ ሁኔታ መካከል ያለውን ልዩነት ለማስተካከል ከፍተኛ



ፍላጎት አለው" ብለዋል ዋና ዳይክተሯ።

ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ በበኩላቸው ምር ቤቱ የትምህርት ተቋማትን እና ኢንዱስትሪውን ለማገናኘት ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ከማኅበሩ ጋር መተባበር የቢዝነስ ትምህርት ቤቶችን እውቀት ማሳደግ እና ከኢንዱስትሪው ጋር ያለውን ግንኙነት ማጎልበት ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

የአፍሪካ ቢዝነስ ትምህርት ቤቶች ማህበር (AABS) ከምር ቤቱ ጋር በመተባበር በሚቀጥለው አመት የ2026 የAABS ግንኙነት ጉባኤ በአዲስ አበባ እንደሚያዘጋጅ ተነስቷል።



ዶ/ር ቀነኒሳ እንዳሉት ከአፍሪካ ፈር ቀዳጅ ተቋማት አንዱ የሆነው ምክር ቤቱ በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እድገት ለማጉላት እና የልምድ ልውውጥ አማራጮችን ለማስተዋወቅና ለመጠቀም ከማህበሩ ጋር መስራቱ የተሻለ አጋጣሚ መሆኑን አንስተዋል።

ምክር ቤቱም ከአፍሪካ ተቋማት ጋር ለጋራ ብልፅግና ዘላቂ ትብብር ለመፍጠር ጥረት እያደረገ ነው ብለዋል።

በሚቀጥለው ዓት በሚካደው ጉባኤ ላይ ከ150 በላይ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ይሳተፉሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ለሀገራዊ ኢኮኖሚም ትልቅ ትርጉም ያለው ጉባኤ እንደሚሆን ጠቁመዋል።



የአፍሪካ ቢዝነስ ትምህርት ቤቶች ማኅበር አባል የሆነው ክቡር ኮሌጅ ፕሬዝዳንት አቶ ደሳለኝ መኩሪያ በበኩላቸው "እንዲህ ያለውን የአፍሪካ ዝግጅት ማዘጋጀቱ ኢትዮጵያ ያለችበትን የኢኮኖሚ እና ልማት ሁኔታ ለማሳየት እና ልምድ ለመለዋወጥ ትልቅ አጋጣሚ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሁለቱ ወገኖች የአፍሪካን ልማት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም በአድቮኬሲ፣ በምርምር እና በአቅም ግንባታ ላይ በጋራ እንደሚሰሩም አረጋግጠዋል።

የአፍሪካ ቢዝነስ ትምህርት ቤቶች ማኅበር መቀመጫውን በደቡብ አፍሪካ ያደረገ የቢዝነስ ትምህርት ቤቶችንና ዩኒቨርሲቲዎችን ያቀፈ ማኅበር ነው።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ፀሐፊ አቶ ፀደቀ ድጋፌ በኢትዮጵያ ከዮርዳኖስ መንግሥት ተጠሪ ዶ/ር ኢማድ መሳልመህ ጋር ተወያይተዋል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ፀሐፊ አቶ ፀደቀ ድጋፌ በኢትዮጵያ ከዮርዳኖስ መንግሥት ተጠሪ ዶ/ር ኢማድ መሳልመህ ጋር ተወያይተዋል።



በኢትዮጵያና በዮርዳኖስ መካከል ያለውን የንግድና የኢንቨስትመንት አጋርነት ለማጠናከር በትብብር መስራት እንደሚገባ በውይይታቸው ተነስቷል።

አቶ ፀደቀ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድና የኢንቨስትመንት አቅም እና እድል ያብራሩ ሲሆን ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለችውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ እና ለአለም አቀፍ ባለሃብቶች ያለውን ማበረታቻ አመልክተዋል።



በኢትዮጵያ በግብርና፣ አይሲቲ፣ ማዕድን፣ ግንባታ እና ቱሪዝምን ጨምሮ በርካታ የኢንቨስትመንት የዮርዳኖስ ባለሀብቶችም በኢትዮጵያ እንደሚሆኑ አመላክተዋል።

እድሎች መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ ጸደቀ መዋዕለ ንዋያውን ቢያፈሱ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ የንግድና ዘር ማኅበራት ለፍሬያማ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በትብብር ለመስራት ዝግጁ ነው ያሉት አቶ ጸደቀ ምክር ቤቱ በተለያዩዘርፎች የዮርዳኖስን ቢዝነሶች ለመደገፍ መዘጋጀቱን አረጋግጠዋል።

ዶ/ር ኢማድ መሳልሜህ በዮርዳኖስና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ እና ቢዝነስ ግንኙነት መጠናከር



እንደሚገባው አመላክተዋል።

እንደ ፋርማሲዩቲካል፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ጨርቃጨርቅ እና ግብርና የመሳሰሉ የዮርዳኖስ ጠንካራ ኢንዱስትሪዎች መሆናቸውን ገልጸው በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ወይም ከኢትዮጵያውያን አቻዎች ጋር በአጋርነት ለመስራት ፍላጎት እንዳላቸው አጽንኦት ሰጥተዋል።



ውይይቱም የሀገራቱን የንግድ ትስስር የዳሰሰ ሲሆን ዮርዳኖስ የኢትዮጵያን ቡና እና ሰሊጥ የምትዛ ሲሆን የተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርት እና የግብርና ምርቶችን ወደ ውጭ እንደምትልክም ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና ከዳኒሽ ኢንሥቲትዩት ፎር ሂውማን ራይትስ ጋር በመተባበር ለንግዱ ማኅበረሠብ " Business and Human rights" በሚል ያዘጋጀው ወርክሾፕ ተካሄደ።

በአዲስ አበባ ራዲሰን ብሉ ሆቴል በሚካሄደው ዚህ ወርክሾፕ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣ ከዳኒሽ ኢንሥቲትዩት ፎር ሂውማን ራይትስ እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የንግዱ ማኅበረሠብ ተወካዮች ተሣታፊ ናቸው።





በወርክሾፑ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የሲቪል፣ ፖለቲካል እና ሶሺዮ ኢኮኖሚክ መብቶች ኮሚሽነር ዶክተር አብዲ ጅብሪል ከሚሽኑ በሚሠራቸው የጥናትና ምርምር፣ የአቅም መገንባት እና የምርምር እና ክትትል ሥራዎች ላይ አብርተዋል።





የንግድ ተቋማት ለሠብአዊ መብቶች መጠበቅ ትልቅ አሥተዋጽኦ እንዳላቸው የጠቀሡት ዶክተር አብዲ ነገር ግን ሥህተት የሚሠሩ እንደሚኖሩ በመጠቆም ይህንን ለማሥተካከል በትብብር መሥራት የጠበቃል ብለዋል።



የአሠሪ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀን ሲዎችን፣ የቡና ዘርፍ ላይ ያሉ ሥራዎችን፣ የግንባታ ሥራዎች ላይ ወዘተ ክትትል መደረጉን ጠቅሠዋል ኮሚሽነሩ ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በጋራ በመሆን ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደሚቻልም ነው የተናገሩ።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቢዝነስ አመራር አካዳሚ ዳይሬክተር አቶ ብሥራት በለጠ በበኩላቸው በምክር ቤቱ የሪፎርም ሥራዎች ዙሪያ ማብራሪያ የሠጡ ሢሆን ከዚህ በፊት የነበሩ ችግሮችን በማሥወገድ ውጤታማ ሥራ መሥራት የሚያሥችል የለውጥ ተግባራት መተግበራቸውን አንሥተዋል። በሌላ በኩል በንግዱ ማኅበረሠብ ዘንድ ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ምክር ቤቱ በትኩረት እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የዳኒሽ ኢንስቲትዩት ፎር ሂውማን ራይትስ (Danish Institute for Human Rights) የምሥራቅ አፍሪካ ተወካይ ዶክተር አጀት ሚሩ አጁሉ ኢንሥቲትዩቱ የሚሠራባቸውን የትኩረት መሥኮች ያብራሩ ሢሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉ የሠብዓዊ መብትና የቢዝነስ ግንኙነት መርሆችና ተሞክሮዎች እንዲሁም በቢዝነስ እንቅሥቃሴዎች ላይ ሥለሚደርሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ገለጻ አድርገዋል።

ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የንግዱ ማኅበረሠብ የላቀ ሚና እንደሚጫዎት ተጠቆመ።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር በመተባበር "Business and Human rights" በሚል የተዘጋጀው ወርክሾፕ ውይይት ተካሂዷል።





በውይይቱም የፍትህ ሚኒሥቴር ተወካዮችን ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትና የንግዱ ማኅበረሠብ ተወካዮች ተገኝተዋል።

በፍትህ ሚኒሥቴር የሰብዓዊ መብቶች ዳይሬክተር አቶ አወል ሱልጣን መሐል



የውይይት መድረኮች የንግድ አሰራሮች ዓለም አቀፍ ሥታንዳርድ እንዲኖራቸውና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ለማድረግ ብሎም ውጤታማ ቢዝነስ መሥራት እንዲቻል አስፈላጊ መሆናቸውን ገልጸዋል።

መመሪያዎችም ግልጽ እንዲደረጉ በማድረግ ረገድ በፍትህ ሚኒሥቴር በኩል ከአንድ ሺ ሶስት መቶ በላይ መመሪያዎች ለማኅበረሠቡ ግልጽ እንዲሆኑ በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ ይፋ መሆናቸውን አንሥተው ይህም በአሠሪ እና በሠራተኛ ወይም በኃላፊ እና ሠራተኛ መካከል መመሪያን መሠረት ያደረገ ግንኙነት እንዲኖር ያሥችላል ብለዋል።

ከህጻናት ጉልበት ብዝበዛ፣ ህገ ወጥ የሠዎች ዝውውር፣ በኢንዱሥትሪዎች በሚሥተዋሉ የመብት ጥሰቶች እንዲሁም ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ትኩረት እንደተሠጣቸው አብራርተዋል።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የህግና ግልግል ማዕከል ዳይሬክተር አቶ ሰላም ሰጠኝ በበኩላቸው የንግዱ ማኅበረሠብ በሚሠራቸው ሥራዎች የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማሥገባት ስታንዳርድ ያላቸውን ሥራዎች መስራት እንደሚገባና ምክር ቤቱም በጉዳዩ ዙሪያ ከአጋር አካላት ጋር በትብብር እንደሚሠራ አብራርተዋል።

በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የሶሺዮ ኢኮኖሚክ መብቶች ዲፓርትመንት ዳይሬክተር ወይዘሪት ሐዊ አሥፋው በበኩላቸው የንግድ ተቋማት የሰብዓዊ መብት መርሆችን አክብረው መሥራት እንዲችሉ ለማድረግ ተከታታይነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ሥራዎች እንደሚሠሩም ተናግረዋል። ተሣታፊዎችም በንግዱ ማኅበረሠብ እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን መካከል ተከታታይ የምክክር ሥራዎች እንደሚያሥፈልጉ ገልጸው ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎችም ተግባራዊ መደረግ እንዳለባቸው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እንዲሁም ከዳኒሽ ኢንስቲትዩት ፎር ሂውማን ራይትስ ጋር በጋራ በመሆን ከንግዱ ማህበረሠብ እንዲሁም ከቢዝነስና የሰብዓዊ መብቶች ጋር በተያያዘ በትብብር እንደሚሠሩ በመድረኩ ላይ ገልጸዋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ንግድ ምክር ቤት አመራር አባላት ''በመትከል ማንሰራራት'' በሚል መሪ ቃል የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር በማረቆ ልዩ ወረዳ ዲዳ ሚዶሬ ቀበሌ በተዘጋጀው ቦታ ላይ አካሂደዋል።



የክልሉ ደንና አካባቢ ጥበቃ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብራሃም መጫ በልዩ ወረዳው ዲዳ ሚዶሬ ቀበሌ አካባቢ በተዘጋጀው ቦታ አሻራቸውን በማኖር የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሃ-ግብርን በይፋ አስጀምረዋል።

አቶ አብራሃም መጫ በዚሁት ወቅት እንዳሉት በአረንጓዴ አሻራ የንግድ ማህበረሰብ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል።



የማረቆ ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ጀማል አማሮ በበኩላቸው የክልሉ ንግድ ምክር ቤት አባላት በመትከል ማንሰራራት በሚል ቃል ሀገራዊ የአረንጓዴ ተከላ መርሐግብር በልዩ ወረዳው ለማካሄድ በመምጣቱ ታላቅ ልባዊ ምስጋና አመስግነዋል።

የክልሉ ንግድ ዘርፍ ማህበር ፕረዚዳንት አቶ ሳኒ ሀሰን በበኩላቸው ምክር ቤቱ ከተመሰረተ የአንድ አመት እድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም አባላቱ በአረንጓዴ አሻራ ልማት የድርሻቸውን ይወጣሉ ማለታቸውን ከልዩ ወረዳው ኮሙኒኬሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።







የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብብ አባፊራ አባጆቢር የንግድ ስራዎች ጅማ ከተማ ሰሙ ቀበሌ በሚገኘውና በድርጅቱ በተያዘው የአረንጓዴ ሥፍራ የችግኝ ተከላ መርኃ ግብር አከናውኗል ::

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብብ አባፊራ አባጆቢር የንግድ ስራዎች ጅማ ከተማ ሰሙ ቀበሌ በሚገኘውና በድርጅቱ በተያዘው የአረንጓዴ ሥፍራ የችግኝ ተከላ መርዐ ግብር አከናውኗል ::







የችግኝ ተከላው በየዓመቱ የሚደረግ ሲሆን ዓመቱን ሙሉ እንክብካቤ የሚደረግለት መሆኑንም ፕሬዚደንቱ ገልፀዋል::

የአዳማ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላትን እና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም (ችግኝ ተከላ) አከናዉኗል ።



ነጋዴዎች፣ የምክር ቤቱ አባላትና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ወደ ዋንጂ ወረዳ በሚወስደው አስፓልት መንገድ ላይ ችግኝ ተክለዋል።



ምክር ቤቱ የአባላትን መብት ከማስጠበቅ እና በነጋዴዎች እና በመንግስት መካከል እንደ ድልድይ ሆ ኖ ከ ማ ገ ል ገ ል ከተመሰረተለት አላማዎች ጎን ለጎን በተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎች ላይም በብቃት እየተሳተፈ ነው ።







የቢሾፍቱ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላን እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሀግብርሩን አካሄደ። የተለያዩ 6700 ችግኞች የተተከሉ ሲሆን የደም ልገሳ እና ለብሾፍቱ ቤተመፀሐፍ የመፀሐፍ ልገሳ ፕሮግራም ተካሂዷል።







የቢሾፍቱ ከተማ ከንቲባ



የቢሾፍቱ ንግድ ምክር ቤት የቦርድ የቦርድ አባላት በመርሃግብሩ ላይ

አባባላት የአትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ የኦሮምያ ንግድ ምክር ቤት ተሳትፎዋል:: (OCCSA)

በኦሮሚያ በሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ ሻዋ ዞን ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች በመትከል ማንሰራራት በምል መሪ አባላትን አስተባብሮ በጋራ በመሆን ችግኞችን በመትከል አሮንጋደ አሻራቸዉን አሳርፈዋሉ ።







Miseensoni mana maree daldalaaf woldaa sektera Godina Shawaa lixaa DHAABUUN DANDAMACHUUDHA JECHUUN Bqiltuu woliin dhaabuun ashaara isani kaa'aniiru

.....

Sagantaa Ashaaraa Magariisa Anaalee Godina Qellam Wallagaa akka itti Fufeetti jira. Sektarri Daldalaa Oromia Magariituu Ijaaruuf gumaacha guddaa taasisaa jiraachuu Agarsiisa!







.....

የአሳላ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሰራተኞች እና የአሳላ ንግድ ማህበረሰብ በመተባበር በመትከል ማንሰራራት መር ቃል የአረንጓዴ ሻራዉን ዛሬ አሳርፈዋል ::



Manni Maree Daldalaa fi waldaalee Seektaraa Godina Qellam Wallagga keessatti argaman Magaalaa Dambi-dooloo fi Aanaa Dalo/Waadaraa Waliin Sagantaa Ashaaraa Magariisaa Bara Ka-na Adoolessaa 5,2017 Gaggeessanii Jiruu. Akka Godina Kanaatti hirmaa-naan Seektarri Daldalaa Biqiltuu dhaabuuf bahanii dhi 320 dha 20 ida'ama 345 yeroo ta'u biqilaa 3500 dhaabuu dandahanii jiru.







የበሸሻ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ አካሄደ።

የበሸሻ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ አካሄደ።

የጅማ ዞን አስተዳደር አቶ ቲጃኒ ናስር፣ የአጋሮ ከተማ እና የጎማ ወረዳ ከፍተኛ አመራሮች እና የንግዱ ማህበረሰብ እንዲሁም የባሻሻ ንግድና





ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት እና የቦርድ አባላት በመረሃ ግብሩ ላይ ተገኝተዋል።

የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት አቶ መሀመድወል ሰይፉ በችግኝ ተከላው ላይ የተገኙትን በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ አመራሮችን እና የንግዱን ማህበረሰብ እንዲሁም ሁሉንም ባለድርሻ አካላትን አመስግነዋል::





ሐምሌ 5 "በመትከል ማንሰራራት"




የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት







የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



የንግድ ምክርቤቱ ራዕይ ፣ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ አምዶች

ራዕይ

“በግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚና አካታች ዕድገት በሁለት የስትራቴጂክ ዘመናት ውስጥ እውን ሆኖ ማየት”

ተልዕኮ

“የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል፣ በመደገፍና ለመብትና ጥቅሙ አድቮኬት በማድረግ፤ ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ፈጠራን በማስተዋወቅና በማበረታታት አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግናን ማምጣት”

ዕሴቶች

- ታማኝነት
- ሙያዊ ብቃት
- አባላት ተኮር ምላሽ ሰጪነት
- ትብብራዊ ጥምረት
- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ማህበራዊ ኃላፊነት

ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች (ስትራቴጂካዊ አምዶች)

1. አድቮኬሲና የፖሊሲ ተፅዕኖ
2. ጠንካራ የአባላት ተሳትፎና ድጋፍ
3. የሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም
4. የአቅም ግንባታና ሥርዓት ማሻሻያ
5. ቴክኖሎጂን ማካትት እና ዲጂታል ሽግግር
6. ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ኃላፊነት
7. ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት
8. ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)

ዋና አዘጋጅ፡-

ተሾመ ዋቅጂራ

ም/ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ

ስማቸው ተበጀ

ፎቶግራፍ

ያለምፍሬ በቀለ

The Ethiopian Chamber of Commerce and Secoral Associations (ECCSA)

ስልክ: +251115514005

ፋክስ: + 251115517699

P. O. Box 517,

ኢ.ሜይል: info@ethiopianchamber.com

ድረ ገጽ: www.ethiopianchamber.com

ቴሌግራም t.me/ethiopiachamber

ትዊተር https://twitter.com/EthiopiaChamber

ፌስ ቡክ: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Youtube: https://www.youtube.com/channel/UCMEZ4TO8dQiIJvk2IQkTxhA

Linkedin(ሊንክዲን):https://www.linkedin.com/company/ethiopianchamber/in